# ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ

## ህይወት ማዳን | አመለካከትን መቀየር

CAREEPILEPSY ETHIOPIA

SAVING LIVES | CHANGING PERCEPTION



# ማውጫ

02 የዋና ዳይሬክተሯ መልዕክት

03 የድርጅት መገለጫ

06 ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ ያከናወናቸው ተግባራት

08 በሚጥል ህመም ላይ ግንዛቤን ማሳደግ

15 በድርጅታችን ድጋፍ የተደረገላቸው ቤተሰቦች

20 ድርጅታዊ ግንኙነቶችን ማዳበር

24 በታማሚዎች የተፃፈ ግጥም

26 አድራሻችን

04 የድርጅታችን ታሪካዊ ዳራ
05 የድርጅቱ ዓላማዎች
07 ለጤና ባለሙያዎች ስልጠና
09 በማህበረሰብ መድረኮች ላይ በመገኘት ስለሚጥል ህመም ማስተማር
10-14 ሰፋፊ የንቅናቄ ዘመቻዎችን ማዘጋጀት - ብሄራዊ የሚጥል ህመም ሳምንት
17 የእጅ ሙያ ክህሎት ስልጠና
18 ማህበራዊ ትስስርን ማጠናከር
19 አጋር ድርጅቶች ጋር መሥራት
20 የኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ በጎ ፈቃደኞች
21 የድርጅቱ አደረጃጀት እና አስተዳደር
22 የድርጅቱ የሰው ሀይል
**23** የኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ የወደፊት ዕቅድ

**የካቲት 2, 2015**
**የኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ**

ማህበረሰቡ ከእምነትና ባህል በተሳሳተ አመለካከት የሚጥል ህመምን እንደ ክፉ መንፈስና እርግማን በመቁጠር የህመሙ ተጠቂን ከማህበራዊ ህይወት ከማግለል ጀምሮ ህክምና እንዳያገኝ በቤት ዉስጥ ደብቆና አስሮ ከማስቀመጥ እስከ አደባባይ አውጥቶ መጣል ድረስ ለከፋ ችግር ይዳረጋሉ።

# የዋና ዳይሬክተሯ መልዕክት

በኢትዮጵያ ዉስጥ በተለያዩ አካባቢዎች እየተዘዋወርኩ ማህበረሰቡ በሚጥል ህመም ዙሪያ ያለውን ግንዛቤና አመለካከት ለመቃኘት ሞክሬያለሁ። ስለ ህመሙ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በመንግስትም ሆነ በግል ተርዐዶ ድርጅቶች ባለመሰራቱ ምክንያት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ከህመሙ የተነሳ ብቻ ሳይሆን የተጨማሪ ችግር ተጠቂዎች በመሆን ለአስከፊ የኑሮ ሁኔታ መጋለጣቸውን መገንዘብ ችያለሁኝ።

በመሆኑም ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ የሚጥል ህመም በአገራችን እያደረሰ ያለውን ግለሰባዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ስፋትና ጥልቀት በመመልከት በህመሙ የሚሰቃዩ ኢትዮጵያውያን የጤና ሁኔታ እንዲሻሻል የህክምና ዕድሎች የሚያመቻች፣ ስለህመሙ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን የተዛባ አስተሳሰብ ለመቀየር ግንዛቤን የሚፈጥር፤ ህመሙ እንዳይከሰት የመከላከል ስራ የሚሰራ፤ የሚጥል ህመምን ማከም የሚችሉ የጤና ባለሙያዎች ቁጥር በጤና ተቋማት ላይ እንዲጨምር ስልጠና የሚሰጥ እንዲሁም የመንግስት ፖሊሲዎች የሚጥል ህመም ታማሚዎችን መብት ልክ እንደማንኛውም ዜጋ ያካተተና ፍላጎታቸውን ከግምት ያስገባ እንዲሆን ትኩረት አድርጎ የሚሠራ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው።

በዓለም ላይ ከ65 ሚሊዮን በላይ ሰዎች ከኢትዮጵያ ጠቅላላ ህዝብ ቁጥር ውስጥ ደግሞ 1.10 ሚሊዮን ገደማ የሚሆኑት ዜጎች የሚጥል ህመም ያለባቸው መሆኑን የጥናት ውጤቶች ያሳያሉ። በኢትዮጵያ ከሚገኙ ታማሚዎች መካከል የህክምና ክትትል የሚያገኙት በአማካኝ 5% ሲሆኑ ቀሪዎቹ 95% የሚሆኑትና የሚጥል ህመም ያለባቸው ዜጎቻችን ወደ ህክምና ተቋማት ሄደው ክትትል የማያደርጉ መሆናቸው ጥናቶች ያመላክታሉ።

ድርጅቱ የ5 ዓመታት የትግበራ ስትራቴጂክ ፕላን በማዘጋጀት የተለያዩ ሚዲያዎችን ተጠቅሞ በሕብረተሰባችን ዘንድ ስለህመሙ የሚስተዋለውን የግንዛቤ ክፍተት መቀነስ እንዲቻል፣ ሰፊ ንቅናቄን መፍጠር፣ የህክምና አገልግሎት ዕድሎችን ማመቻቸት፣ ህክምናው በሁሉም ጤና ማዕከላት እንዲሰጥ ማገዝ፣ ነፃ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣ መድሃኒታቸውን መውሰድ እንዳያቋርጡና አቅርቦቱም እንዲስፋፋ እገዛ በማድረግ የታሰበውን አሳክቷል። በተጨማሪም የሚጥል ህመም ያለባቸውን ሰዎችና ቤተሰቦቻቸውን በማሰባሰብ ብሄራዊ ማህበር መመስረት፣ ታማሚዎቹ የሙያ ክህሎት ስልጠና እንዲሁም ወላጆቻቸው በገቢ

ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ የሚጥል ህመም ያለባቸው ሰዎች ጤናማ፣ አምራች፣ ከመገለልና መድሎ ነጻ ሆነው ማየት የሚል ራዕይ ይዞ በጥቅምት ወር 2008 ዓ.ም ነው ስራ የጀመረው።

ማስገኛ ስራ እንዲሰማሩ ማቋቋም፣ የሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤትና ሌሎች ድርጅቶች ትኩረት ለሚጥል ህመም እንዲሰጡ የቅስቀሳ ስራ ከተሰሩት ተግባራት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ውድ አንባቢያን የሚጥል ህመምን በህክምና ድጋፍ መቆጣጠር እንደሚቻል ግንዛቤ ያለው የህብረተሰብ ቁጥር በእጅጉ አናሳ በመሆኑ በየአካባቢያችን በችግሩ የተጎዱ ወገኖቻችን ወደ ህክምና እንዲሄዱ በማበረታታት፣ ከመገለልና መድሎ ነጻ በማድረግ፣ አምራች ዜጋ እንዲሆኑ አስፈላጊውን እገዛ እንድታደርጉላቸው በፈጣሪ ስም እጠይቃለሁ።

ትኩረት ለሚጥል ህመም!



ወ/ሮ እናት የዉነቱ
የህብረተሰብ ጤና ባለሙያ
መሥራች እና ዋና ዳይሬክተር



# የድርጅት መገለጫ

የሚጥል ህመም ያለባቸው ሰዎች ከሚገጥሟቸው ተግዳሮቶች መካከል በዋናነት፡- ከህመሙ እና ተያያዥነት ካላቸው የጎንዮሽ ጉዳቶች ጋር መኖር፣ ጥራት ያለውና የማያቋርጥ የሕክምና አቅርቦት አለመኖር፣ ሕመማቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል አዳዲስ የመድኃኒት ምርቶች አለመኖር፣ የመድኃኒት ዋጋ ንረት እና የአቅርቦት ውስንነት፣ ከህመሙ የተነሳ ለቅድመ ሞት ተጋላጭ መሆን እንዲሁም መገለልና መድልዎ ናቸው።

ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ እንዲሁም የሚጥል ህመም ያለባቸው ሰዎች ጤናማ፣ አምራች፣ ከመገለልና መድሎ ነፃ ሆነው ማየት የሚል ራዕይ ይዞ በሀገራችን ተገቢውን የህክምና ትኩረት ሳይሰጣቸው በሚጥል ህመም ለዘመናት ሲሰቃዩ የቆዩ ዜጎችን ህይወት ለመታደግ የተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው።

## የድርጅታችን ዝርዝሮች

ሀ) የድርጅቱ ስም ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ

ለ) የድርጅቱ ተጠሪ: እናት የዉነቱ

ሐ) ዋና ዳይሬክተር: እናት የዉነቱ

መ) የድርጅቱ ሕጋዊ ሁኔታ-

- የምዝገባ ባለስልጣን በኢትዮጵያ ሲቪክ ማህበራት ኤጀንሲ የተመዘገበ
- የምዝገባ ቁጥር: 3380
- የተቋቋመበት ዓመት-: ጥቅምት 2008

ሠ) መገኛችን

ተንቀሳቃሽ ስልክ: +2519 1163 3077

የመስመር ስልክ: +2511 16 69 44 55

ረ) ኢሜይል - ceo@careepilepsyethiopia.org

ረ) የፕሮጀክት ተግባራት

- የሚጥል ህመም ህክምናን ተደራሽ ማድረግ፣ ግንዛቤን ከፍ ማድረግ እንዲሁም የታማሚዎችን አቅም ማጎልበት





# የድርጅታችን ታሪካዊ ዳራ

ኤርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ የሚጥል ህመም ያለባቸው ሰዎች በሀገራችን ተገቢውን የህክምና ትኩረት ሳይሰጣቸው በሚጥል ህመም ለዘመናት ሲሰቃዩ የቆዩ ከ1.10 ሚሊዮን በላይ የሆኑ ዜጎችን ህይወት ለመታደግ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ተመዝግቦ በ2008 ዓ.ም በወ/ሮ እናት የዉነቱ የተቋቋመ መንግስታዊ እና ሀይማኖታዊ ያልሆነ ግብረሰናይ ድርጅት ሲሆን የሚጥል ህመም ላለባቸው እና ለቤተሰቦቻቸው የሚሰራ በኢትዮጵያ ውስጥ በመስኩ የመጀመሪያው በጎ አድራጎት ድርጅት ነው:: የድርጅቱ መስራች የሆኑት ወ/ሮ እናት የዉነቱ ከሚጥል ህመም ጋር የሚኖሩ፣ በትውልድ ኢትዮጵያ ሲሆኑ በሙያቸውም የህብረተሰብ ጤና ባለሙያ፣ መምህርት እንዲሁም የሚጥል ህመም ላለባቸው ሰዎች የመብት ተሟጋች ናቸው::

ወ/ሮ እናት የውነቱ በ1986 ዓ.ም ተወልደው ካደጉበት ከአዲስ አበባ ወደ እንግሊዝ ሀገር ላጋጠማቸዉ የሚጥል ህመም ፈዉስ ለማግኘት እግረ መንገዳቸዉንም የመጀመሪያ ዲግያቸዉን ለመማር በለጋ እድሜያቸዉ ሄደው ከአመታት የትምህርት ቆይታ በኃላ ከዓንድሩስ ዩኒቨርሲቲ (Andrews University) በቢዝነስ ማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪያቸዉን አገኙ:: ሁለተኛ ዲግሪያቸዉን እዛዉ ሀገረ እንግሊዝ በመቀጠል በህብረተሰብ ጤና (Public Health MPH) ወሰዱ:: በለንደን ውስጥ በቆዩበት ጊዜ በሴቶች እና በህፃናት የጤና አጠባበቅ አገልግሎት ዘርፍ፣ በሆስፒታል አስተዳደር እና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ላይ በሙያቸው ሲሰሩ ቆይተዋል::

ወ/ሮ እናት የዉነቱ ምንም እንኳን የሚጥል ህመም ያለባቸው ቢሆኑም ይኖሩበት በነበረው በእንግሊዝ ሀገር አስፈላጊውን ሕክምና እና መድሃኒት ለማግኘት እድሉን በማግኘታቸው ህመማቸውን ተቆጣጥረው መማር፣ ቤተሰብ መመስረት እና ልጅ መውለድ የቻሉ ጠንካራ ሴት ሲሆኑ በአሁኑ ጊዜ የህይወታቸው ጥሪ የሆነውን የሚጥል ህመም ያለባቸውን ሰዎች በሀገራቸው እየረዱ ይገኛሉ::

ይህ በጎ አድራጎት ድርጅት የተመሰረተበት አብይ ምክንያት ወ/ሮ እናት የዉነቱ በሚጥል ህመም ለ30 ዓመታት ያጋጠማቸውን ፈታኝ ችግሮችን (አካላዊ እና ስሜታዊ) አሸንፈው ስኬታማ ሕይወትን በመኖራቸው ታሪካቸውን ተስፋ ለቆረጡ እና በሚጥል ህመም ለተሸነፉ ማንቂያ ተስፋ እንዲሆናቸውና ሌሎች የሚጥል ህመም ታማሚዎች ከሚጥል ህመም ጋር ህልማቸዉን እውን አድርገው ስኬታማ ህይወት መኖር እንደሚችሉ እንዲገነዘቡ፣ በራሳቸው እንዲተማመኑ ለማድረግ እና ለማስተማር ነው:: ድርጅቱ በሃገራችን ግንባር ቀደም እንደ መሆኑ ይዞ በተነሳው አላማ በህመሙ ተጠቂ ወገኖችን፣ በጤና ሚኒስቴር፣ በክልል ጤና ቢሮ፣ በክፍለ ከተማ ጤና ጽህፈት ቤት፣ በአገልግሎት ሰጭ ተቋማትና በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተቀባይነትን አግኝቶ አመርቂ ስራ በመስራት ላይ ይገኛል።

### የድርጅታችን ተልእኮ፣ ራዕይ፣ እሴቶች እና ዓላማዎች

### ራዕያችን

የሚጥል ህመም ያለባቸው ሰዎች ጤናማ፣ አምራች፣ ከመገለልና መድሎ ነፃ ሆነው ማየት።

### ተልእኳችን

በህመሙ የሚሰቃዩ ኢትዮጵያውያን የጤና ሁኔታ እንዲሻሻል፣ የህክምና እድሎችን ማመቻቸት፣ የመድሃኒት አቅርቦትን ማስፋፋት ለአደጋ ተጋላጭነትን መቀነስ፣ ስለህመሙ በህብረተሰቡ ውስጥ ግንዛቤ መፍጠር፣ ደህንነትን ማረጋገጥ ህይወትን መታደግ እና አመለካከትን መቀየር።

### እሴቶቻችን

- ግልፅነትን ማረጋገጥ
- አሳታፊነት
- ለታማሚዎች ክብር መስጠት
- ታማሚውን የለዉጥ አራማጅ ማድረግ
- ዘላቂ ለዉጥ ለማምጣት ተቀናጅቶ መስራት

የአገልግሎታችን ተጠቃሚዎች ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ሲሆኑ በተለይም የሚጥል ህመም ያለባቸዉ ሴቶች፣ ወንዶች፣ ልጆች፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦቻቸው የጤና ተቋማት፣ የጤና ባለሙያዎች እንዲሁም መምህራኖችን ያጠቃልላል::

## የድርጅቱ ዓላማዎች

የሚጥል ህመም ያለባቸው ሰዎች በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ ይኖራሉ በዋናነት ከህመሙ እና ተያያዥነት ካላቸው የጎንዮሽ ጉዳቶች ጋር መኖር ፣ ጥራት ያለው የማያቋርጥ የሕክምና አቅርቦት አለመኖር ፣ ሕመማቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል መድሃኒት አቅርቦት በስፋት አለመኖር ፣ የመድኃኒት ዋጋ ንረት ፣ ከህመሙ የተነሳ ለቅድመ ሞት ተጋላጭ መሆን እንዲሁም መገለልና መድልዎ ናቸው። የሚጥል ህመም ያለባቸው ሰዎች እና ቤተሰባቸው ብዙ ጊዜ የተለያዩ የማኅበረሰብ አገልግሎቶች ይፈልጋሉ ከእነዚህ ውስጥ ድርጅቱ ትኩረት አድርጎ የሚሰራቸው ሰራዎች እንደሚከተለዉ ናቸዉ።

ዓላማዎቻችን የሚከተሉት የትኩረት አቅጣጫዎች: -

- የሚጥል ህመም ታማሚዎች እና ቤተሰቦቻቸውን ደኅንነት ማሻሻል፣
- የሚጥል ህመም ሕክምና ተደራሽነትን ማስፋት፣
- በህብረተሰቡ ውስጥ ስለሚጥል ህመም ያለውን የተዛባ አመላከከት መለወጥና ይበልጥ አዎንታዊ ግንዛቤ መፍጠር፣
- የሚጥል ህመም ያለባቸውን ሰዎች ሙሉ ደህንነት ማሻሻል እና ራሳቸውን እንዲችሉ አቅማቸውን ማጎልበት፣
- በብሔራዊ ደረጃ የሚጥል ህመምን የመከላከል እርምጃዎችን ማሻሻል
- ለታማሚዎች መብት መሟገት እና ድርጅታዊ ግንኙነቶችን ማዳበር

## የድርጅቱ የስራ ፍልስፍና

የኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ የስራ ፍልስፍና መሠረት ያደረገው በዓለም ጤና ድርጅት ውስጥ ከተዘረዘሩት መሰረታዊ መርሆዎች የሚመነጨው "…ጤና ለሁሉም የሰው ልጅ መሠረታዊ ሰብአዊ መብት ነው" የሚለው እና "የሰው ልጅ ሁሉ ሲወለድ ነጻ፣ በክብርና በመብትም እኩልነት ያለው ነው። የተፈጥሮ ማስተዋልና ሕሊና ስላለው አንዱ ሌላውን በወንድማማችነት መንፈስ መመልከት ይገባዋል" የሚለው በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች አንቀጽ 1 ላይ በተገለጸው መሠረት ነው። ስለዚህም፡-

- የሚጥል ህመም ያለባቸው ሰዎች የሕክምና እንክብካቤ እና መድኃኒት የማግኘት መብት አላቸው፣
- የሚጥል ህመም ያለባቸው ሰዎች ትምህርት የመማር፣ ሥራ የመያዝ እና መገለልና መድልዎ ሳይደርስባቸው የመኖር ሰብዓዊ መብት አላቸው፣
- የሃገር ሽማግሌዎች፣ የእምነት አባቶች እና ህብረተሰብን መሠረት ያደረጉ ድርጅቶች የተሻለ ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ ሚና መጫወት አለባቸው፣
- ስለሚጥል ህመም ያለዉን የተሳሳተ አመለካከት ለመለወጥ ባህልን ያማከለ ትምህርታዊ መልእክቶች መሰጠት አለባቸው፣
- አጋር ድርጅቶች ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ ሃላፊነት አለባቸው።

## አገልግሎታችን የሚሰጥበት ቦታዎች

ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ በአዲስ አበባ እና በሁሉም ክልሎች ከከተማ እስከ ገጠር አካባቢዎች በአጠቃላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው።

ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ ዓላማዉን ለማሳካት የታማሚዉን፣ የቤተሰቡን እና የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማጠናከር ከመንግስት፣ ከአጋር ድርጅቶችና ከበጎ ፈቃደኞች ጋር ዘላቂነት ያለዉ ስራ አብሮ ይሰራል።

1






# ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ እስካሁን ያከናወናቸው ተግባራት

ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በሀገራችን ውስጥ በሚጥል ህመም ላይ ያለውን ችግሮች ለመቅረፍና ታማሚዎቹንም በማገዝ አምራችና ጤናማ ዜጋ እንዲሆኑ ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። ድርጅቱ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ስራዎችን ያከናወነ ሲሆን ከነዚህም መካከል በዋነኝነት የሚጠቀሱት:-

## 1. የሚጥል ህመም ህክምና አገልግሎት ማመቻቸት

የሚጥል ህመም ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እና ተደራሽነት ያለው መሆን እንዳለበት ድርጅታችን በጽኑ ያምናል። ለዚሁ ዓላማ የድርጅታችን አስተዳደር ለሚጥል ህመም ታማሚዎች እና ቤተሰቦቻቸው ከፍተኛ ፍቅርና ርህራሄ በተሞላበት መንገድ የተለያዩ አገልግሎቶችን እየሰጠ ይገኛል።

### ነጻ የህክምና አገልግሎት መስጠት፣

ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ታማሚዎች በድርጅቱ በኩል በነርሶች እና በነርቭ ሐኪሞች የሚመራ ነፃ የሚጥል ህመም ህክምና አግኝተዋል።

### የመድኃኒት አቅርቦት

ድርጅቱ የጤና መድህን ሽፋንን በየአመቱ ከመክፈልና ከማሳከም ባለፈ በሚጥል ህመም መድኃኒት አቅርቦት እጥረት እና የዋጋ ውድነት ምክንያት አቅም ለሌላቸው ታማሚዎች ለመጠባበቂያነት የሚሆን የመድሀኒት እገዛ የሚያደርግ ሲሆን እንዲሁም የሚጥል ህመም መድሀኒት የሚያቀርቡ መድሀኒት ቤቶችን መረጃውን በመሰብሰብ መድሀኒቱን በአቅራቢያቸው ሄደው እንዲገዙ መረጃ ስጥቷል።

### የነርቭ ህመም ምርመራዎችን ማመቻቸት

የሚጥል ህመም ያለባቸዉ ሰዎች በአንጎል ውስጥ ያልተለመዱ የኤሌክትሪክ እንቅስቃሴ አላቸው ስለሆነም የኢኢጂ (EEG) እና ኤምአርአይ (MRI) ምርመራ ሲያደርጉ ውጤቶቹ ሐኪሞች የሚገነዘቧቸውን የአንጎል ሞገድ ሁኔታዎችን ያሳያሉ። ድርጅታችን ይህንን ተገንዝቦ የኢኢጂ (EEG) ማሽን ከውጭ ሀገር በማስመጣት ታማሚዎች አገልግሎቱን በነፃ የሚያገኙበትን መንገድ አመቻችቷል።



# የሚጥል ህመምን ማከም የሚችሉ የጤና ባለሙያዎች ቁጥር በጤና ተቋማት ላይ እንዲጨምር ስልጠና በመስጠት ላይ

–

አዲስ አበባ





የሚጥል ህመም ያለባቸው ሰዎች የተሻለ ህክምና እንዲያገኙ በሚዛን አማን ከተማ ለቤንች ማጂ ዞን ወረዳ ጤና ጽ/ቤት ሃላፊዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡









# በሚጥል ህመም ላይ ግንዛቤን ማሳደግ

የሚጥል ህመም ህክምና የታማሚውን ቤተሰብና የህብረተሰቡን ድጋፍ ይጠይቃል። ይህ ድጋፍ በተገቢው ሁኔታ ሊተገበር የሚችለዉ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ስለህመሙ ያለው የተሳሳተ አመለካከትና ግንዛቤ ሲለወጥ፣ ህሙማን በወቅቱ ወደ ጤና ድርጅቶች ሄደው ምርመራና ህክምና ሲያገኙና በህመሙ ምክንያት የሚከሰተው የአካል ጉዳት መቀነስ ሲቻል ነው።ስለሆነም ይህን በሕብረተሰባችን ዘንድ ስለህመሙ የሚስተዋለውን የግንዛቤ ክፍተት መቀነስ እንዲቻል ሰፊ ንቅናቄ በመፍጠር ጉዳዩ ትኩረት እንዲያገኝ ድርጅታችን ይሰራል። የማግለል ችግርን ለመቀነስ ብዙ ትግል፣ ትዕግስት እና ለህብረተሰቡ ትክክለኛ ግንዛቤ ማስጨበጥ የሚያስፈልግ በመሆኑ ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያም ይህን የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት ለመስጠት የተለያዩ መንገዶች ይጠቀማል ከነዚህም መካከል

## በተለያዩ ት/ቤቶች ውስጥ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ሲሰጥ

በኢትዮጵያ የሕፃናትንና የወጣቶችን የሚጥል ህመም ችግሮችን ለመፍታት ለተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎች እና ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ የሚጥል ህመም ምን እንደሆነ፣ እንደማንኛውም ህመም በመድሀኒት መቆጣጠር እንደሚቻል፣ የመጀመሪያ እርዳታ እንዴት እንደሚሰጥ፣ ተላላፊ ወይንም የልክፍት ሰለባ አለመሆኑን እና የሚጥል ህመም ያለባቸዉን ተማሪዎች ሰለሚያስፈልጋቸዉ ድጋፍ እና እንክብካቤ ትምህርትና ስልጠና ይሰጣል::  እስካሁን ድረስ ለተማሪዎች እና ለመምህራን የተሰጠው ሥልጠና አብዛኞቹ የሚጥል ህመም ያለባቸው ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ እንደሚችሉ እንዲገነዘቡ ረድቷቸዋል ::






በየካ ፣ ኪሮክስ ፣ ቦሌ እና ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተሞች ውስጥ ላሉት 35 ጤና ጣቢያዎች እንዲሁም 8 ሪፈራል ሆስፒታሎች ውስጥ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ሰለህመሙ፣ ለህሙማኑ ሊደረግ ሰለሚያስፈልገዉ ድጋፍ እና የመጀመሪያ እርዳታ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ተሰጥቷል::

## በጤና ማዕከሎች እና በሆስፒታሎች ላይ ማስተማር

በሚጥል ህመም ላይ የሚስተዋለውን የእውቀት ክፍተት ለመቀነስ በአማርኛ ፣ በትግርኛ እና በኦሮምኛ የተፃፉ ትምህርታዊ በራሪ ወረቀቶች፣ ፖስተሮች እና የድምፅ መልእክቶች የመሳሰሉት የትምህርት ቁሳቁሶች በሪፈራል ሆስፒታሎች ፣ ጤና ጣቢያዎች ፣ ትምህርት ቤቶች እና መላ ህብረተሰቡን ለመድረስ በጎዳና ላይ ተሰራጭተዋል::

# በማህበረሰብ መድረኮች ላይ በመገኘት ስለሚጥል ህመም ማስተማር



በስፖርት ውድድር ቦታዎች እና የእድር አባላትን በመደበኛ ጉባኤዎቻቸው ላይ በመገኘት ስለህመሙና ለህሙማኑ ሊደረግ ስለሚያስፈልገዉ ድጋፍና የመጀመሪያ እርዳታ ትምህርት እነርሱም ለሌሎች ትምህርቱን እንዲሰጡ ስልጠና መስጠት::



የማህበረሰብ መድረኮች ከምንላቸው መካከል እድሮች ሰዎች ተገናኝተው ማህበራዊ አገልግሎቶችን ከሚያገኙበት መንገዶች አንዱ ነው፡፡ በእነዚህ መድረኮች ላይ በመገኘት ስለሚጥል ህመም ማስተማር እስከታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ድረስ የመድረስ እድል በመኖሩ ስለሚጥል ህመም ሰማስተማርና የሚፈለገውን ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ ስራ ይሰራል፡፡









# ሰፋፊ የንቅናቄ ዘመቻዎችን ማዘጋጀት

## 1ኛዉ ብሄራዊ የሚጥል ህመም ሳምንት ፕሮግራም - ከግንቦት 14 -20, 2008



ብሄራዊ የሚጥል ህመም ሳምንት በአመት አንድ ጊዜ በአዲስ አበባ እና በክልል ከተሞች ላይ የሚዘጋጅ ሲሆን ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የሚሳተፍበት፣ የመገናኛ ብዙሀንን እንደ መሣሪያ በመጠቀም ትምህርት የሚሰጥበት፣ በሚጥል ህመም የሚወድቅ ሰውን እንዴት መርዳት እንደሚቻል የሚያሳይ ትዕይንት በወጣቶች የሚቀርብበት፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ የእግር ጉዞ የሚደረግበት እና የተለያዩ ዜማዎችንና መልዕክቶችን በማስተላለፍ ህብረተሰቡን የማነቃቃትና ግንዛቤ የመፍጠር ስራ የሚሰራበት ሳምንት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ህብረተሰቡ በብዛት በሚዘዋወርባቸው ስፍራዎች በመገኘት በሙዚቃና ውዝዋዜ፣ አጫጭር ድራማዎችና ቀልዶች በማጀብ ስለሚጥል ህመም ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ስራዎች የሚከናወኑበት ፕሮግራም ነው፡፡

### ዓመታዊ ብሄራዊ የሚጥል ህመም ሳምንት አላማዎች

- የሚጥል ህመምን በህክምና ድጋፍ መቆጣጠር እንደሚቻል ግንዛቤ በመፍጠር በየአካባቢያችን በችግሩ የተጎዱ ወገኖቻችን ወደ ህክምና እንዲሄዱ በማድረግ፣ ከመገለልና መድሎ ነጻ ሆነው አምራችና ሁሉንም ስራ መስራት እንደሚችሉ እውቅና ለመስጠት፡፡

- መንግስት ለሚጥል ህመም ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የህክምና ተቋማትን በመደገፍ፣ በቂ የመድሃኒት አቅርቦት በማድረግ እና ለነርሶች ስልጠና በመስጠት ላይ እንዲሰራ ድምፃችንን ማሰማት፡፡

# 2ተኛዉ ብሔራዊ የሚጥል ህመም ሳምንት

# ከሰኔ 5-11, 2009 ዓ.ም.

## የመዝጊያ ስነ-ስርዓት የእግር ጉዞ በሚዛን አማን ከተማ










ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ 2ኛውን ብሄራዊ የሚጥል ህመም ሳምንት በቤንች ማጂ ዞን ሚዛን አማን ከተማ ከፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከደቡብ ክልል ጤና ቢሮ ጋር በጋራ በመተባበር አከናውኗል። ብሔራዊ የሚጥል ህመም ሳምንት ስለሚጥል ህመም ግንዛቤ ለማሳደግ ፣ የመጀመሪያ እርዳታ አሰጣጥ ለማስተማር እና የሚጥል ህመም ካለባቸው ሰዎች ጋር ለመገናኘት ሰፊ እድል የከፈተና ውጤታማ ዝግጅት ነበር፡፡ በዚህም ፕሮግራም ላይ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተወካይ ፣ ከደቡብ ክልል ጤና ቢሮ ሃላፊዎች ፣ ከቤንች ማጂ ዞን አስተዳደር እና ጤና ቢሮ ሃላፊዎች፣ በዙሪያዉ ካሉ የወረዳ አስተዳዳሪዎች ፣ ታማሚዎች እና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ህብረተሰቡ በተዘጋጀው የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም ላይ ተሳትፈዋል።

# 3ተኛዉ ብሔራዊ የሚጥል ህመም ሳምንት ከየካቲት 5-11, 2010 ዓ.ም.

የየካ ክፍለ ከተማ ጤና ጽ/ቤት ዳይሬክተር እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ዳይሬክቶሬት የመምሪያ ሃላፊው የሚጥል ህመም አገልግሎትን ለማሻሻል እና ስለሚጥል ህመም ግንዛቤ ለማሳደግ ያላቸውን ቁርጠኝነት ለማሳየት ፕሮግራሙን በጋራ በማዘጋጀት የተሳተፉ ሲሆን እንዲሁም በቀኑ ተገኝተው ንግግር አድርገዋል::

## የመዝጊያ ስነ-ስርዓት የእግር ጉዞ በአዲስ አበባ ዳያስፖራ አደባባይ - መገናኛ










# 4ተኛዉ ብሔራዊ የሚጥል ህመም ሳምንት ከየካቲት 4- 10 .2011 ዓ.ም. የመዝጊያ ስነ-ስርዓት በአዲስ አበባ፡መስቀል አደባባይ

ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ ከኢትዮጵያ የነርቭ ሃኪሞች ማህበር ጋር በመተባበር **3**ውን ብሔራዊ የሚጥል ህመም የግንዛቤ ማስጨበጫ ሳምንት, **2010** በመስቀል አደባባይ ሲያከብሩ







4ተኛው ብሔራዊ የሚጥል ህመም ሳምንት ጋዜጣዊ መግለጫ, የካቲት 4, 2011 የመዝጊያ ሥነ ሥርዓት, የካቲት 10, 2011 በአዲስ አበባ





# 5ኛዉ ዓመታዊ ብሄራዊ የሚጥል ህመም ሳምንት ፕሮግራም ከየካቲት 2 -8, 2012 2012










**የካቲት 8, 2012 የግንዛቤ ማስጨበጫ የእግር ጉዞ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲት 6ኪሎ መነሻውን አድርጓል**

የሚጥል ህመም ሳምንት ግንዛቤ በመፍጠር መገለልን እና አድልዎን ለማስወገድ የተጀመረ ዘመቻ ነው። በሳምንቱ ውስጥ ከተደረጉ ፕሮግራሞች መካከል የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎች እና ቃለመጠይቆች እንዲሁም በሙዚቃ የታጀበ የግንዛቤ ማስጨበጫ የእግር ጉዞ ይጠቀሳሉ:: በእግር ጉዞው ፕሮግራሙ ላይ ታማሚዎች፣ ቤተሰቦቻቸው እና ህብረተሰቡ በተገኙበት በደማቅ ሁኔታ ተከናውኗል፡፡

**በኮቪድ ምክንያት ከየካቲት 8, 2012 የግንዛቤ ማስጨበጫ የእግር ጉዞ በኋላ ሌላ አላደረግንም፡፡**



የሚጥል ህመም ያለባቸው ሰዎች እና ቤተሰቦቻቸው ከህክምና አገልግሎቶች ባሻገር ብዙ የተለያዩ የማኅበረሰብ አገልግሎቶች እና የኢኮኖሚ ድጋፍ ይፈልጋሉ። ይህንንም ለሟሟላት የሕመምተኞችን የኑሮ ሁኔታና አጠቃላይ ደህንነት ለማሻሻል ድርጅታችን አቅም ለሌላቸው ታማሚዎችና ቤተሰቦቻቸዉ የምግብ እና የቁሳቁስ ድጋፍ ያደርጋል።

## በድርጅታችን ድጋፍ የተደረገላቸው ቤተሰቦች





# ማህበራዊ ትስስርን ማጠናከር







**ወርሃዊ አቻላቻ መደጋገፍ እና  የጋራ የምክክር መድረከ**

ታማሚዎች እንዲሁም ቤተሰቦቻቸው በየጊዜው እየተገናኙ በሚያጋጥማቸው የግልና የጋራ ጉዳዮቻቸው ላይ እንዲወያዩ፥ የጋራ ችግሮችን እንዲቀርፉ፥ የአቻ ላቻ ግኑኝነትን እንዲያጠነክሩና እንዲደጋገፉ መድረክ በመፍጠር ወርሀዊ አቻላቻ ስብሰባና ሳምንታዊ የኑ ቡና ጠጡ ፕሮግራሞች ያዘጋጃል።

**ኑ ቡና ጠጡ ፕሮግራም**

ኑ ቡና ጠጡ ፕሮግራም  ላይ በመሳተፍ የጋራ እና የግል ችግሮቻቸውን በግልጽ በመወያየት መፍትሄ እንዲያገኙ ለማስቻል የታሰበ ሲሆን ፕሮግራሙም በየሳምንቱ እሮብ በኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ ቢሮ ከጥዋቱ 4፡00 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል።

**የስነልቦና ማማከር አገልግሎት**

ታማሚዎች የሚደርስባችውን ማህበራዊ ተጽዕኖ (ችግሮች) መፍታት እንዲችሉ እና እንደማንኛውም ሰው መስራት እና ማድረግ የሚፈልጉትን ነገር መከወን እንዲችሉ የሚያግዛቸውን የስነ-ልቦና ድጋፍ የሚያገኙበት የምክር አገልግሎት ሰጥቷል።

**የምክርና የመረጃ አገልግሎት**

በሚጥል ህመም ታማሚ ለሆኑ ጭንቀታቸውን በመጋራት እንዲሆም ጤንነታቸውን ለመጠበቅ የሚጥል ህመም የሚሰጥባቸውን ሆስፒታሎችና የመድሀኒት ቤቶች ዝርዝር ለታካሚዎች በስልክ እና በአካል የመረጃ አገልግሎት ተሰቷል።



በሚጥል ህመም ዙሪያ ያለውን መገለልን እና መድልዎን ለማጥፋት ከእምነት አባቶች እና ከማህበረሰብ መሪዎች ጋር  በአዲስ አበባ እና በሚዛን ከተማ የተደረገ ውይይት።







# የእጅ ሙያ ክህሎት ስልጠና እየተሰጣቸው ያሉ ሕመምተኞች



በታማሚዎች የተሰራ የእጅ ሥራ



















የድርጅታችን ሰራተኞች ታካሚዎችን እና ቤተሰቦቻቸውን ቤት ለቤት በመጎብኘት ላይ

# ስለሚጥል ህመም በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው የተዛባ አመለካከት እንዲቀየር ግንዛቤ መፍጠር



ወርሃዊ አቻላቻ መደጋገፍ እና የጋራ የምክክር መድረክ

የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ስለሚጥል ህመም ያለው የተሳሳተ ግንዛቤ ነው። ይህም ለህመሙ መንስኤ ነው ተብሎ የሚታመነው እርኩስ መንፈስ፣ ከፈጣሪ ቁጣ እና ከተለያዩ ነገሮች ጋር በማያያዝ ስለሆነ ሰዎች የጤና አገልግሎት ሰጭዎች ጋር ሄደው ህክምና እንዳያገኙ ትልቅ እንቅፋት ሆኗቸዋል። ከዚህም ባሻገር ህመሙ ያለባቸው ሰዎች ላይ መገለልና መድሎ እንዲደርስባቸው አድርጓል።



የሚጥል ህመም ህክምና የታማሚውን ቤተሰብና የህብረተሰቡን ድጋፍ ይጠይቃል። ይህ ድጋፍ በተገቢው ሁኔታ ሊተገበር የሚችለዉ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ስለህመሙ ያለው የተሳሳተ አመለካከትና ግንዛቤ ሲለወጥ፣ ህሙማን በወቅቱ ወደ ጤና ተቋማት ሄደው ህክምና ሲያገኙና በህመሙ ምክንያት የሚከሰተውን የአካል ጉዳት መቀነስ ሲቻል ነው። ስለሆነም ይህን በሕብረተሰባችን ዘንድ ስለህመሙ የሚስተዋለውን የግንዛቤ ክፍተት መቀነስ እንዲቻል ድርጅታችን ማህበረሰብ ተኮር ንቅናቄ በማካሄድ በሚጥል ህመም ላይ ግንዛቤን ያስጨብጣል። የማግለል ችግርን ለመቀነስ ብዙ ትግል፣ ትዕግስት እና ለህብረተሰቡ ትክክለኛ ግንዛቤ ማስጨበጥ የሚያስፈልግ በመሆኑ ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያም ይህን የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት ለመስጠት የሚከተሉትን መንገዶች ይጠቀማል።




- ታማሚዎች ስለህመማቸው በቂ ዕውቀት እንዲኖራቸው እና እራሳቸዉን እንዴት ከአደጋ እንደሚከላከሉ ትምህርት ይሰጣል፣
- በተጨማሪም ፣ ሕመምተኞች እና ቤተሰቦች ስለሚጥል ህመም እና ስኬታማ ሕይወት እንዴት እንደሚኖሩ የራስ እገዛ ስልቶችን ያስተምራል፣
- ከሚጥል ህመም ጋር አብሮ መኖርን፣ ህክምና፣ የአካል እና የስነ፡ልቦና ተፅእኖዎችን እንዲሁም የሚያስፈልጉትን የአኗኗር ለውጦችን የግለሰቦችን ራስን ማስተዳደር ችሎታ ለማዳበር እናስተምራለን፣
- ስለሚጥል ህመም የሚያስተምር መጽሐፍት እና በራሪ ጽሑፎችን ይሰጣል፣
- ህመምተኞች በሚጥል ህመም እንክብካቤቸው ውስጥ እንዴት መሳተፍ እንዳለባቸው መንገዶችን ያስተምራል
- ስለሚጥል ህመም ትምህርት እና የመጀመሪያ እርዳታ ለህመምተኛ ቤተሰቦችና ለህብረተሰቡ ስልጠና ተሰጥቷል::

# የአድቮከሲ ስራ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር መሥራት

## ለታማሚዎች መብት መሟገት እና ድርጅታዊ ግንኙነቶችን ማዳበር

በኢትዮጵያ በሚጥል ህመም ዙሪያ ላሉ ችግሮች መፍትሄዎቹ በጣም የተወሳሰቡና አንድ ድርጅት ብቻዉን ሊፈታው የማይቻል ነው። ስለሆነም ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት፣ አዳዲስ ሀሳቦችን ለማመንጨት እና መፍትሄዎችን ለማምጣት ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች፣ ከሌሎች መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ በበጎ አድራጎት አገልግሎት ላይ ከሚሳተፉ በጎ ፈቃደኞች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ምንጊዜም ግንኙነቱን አጠናክሮ በትብብር ይሠራል። ይህንንም የምናሳካበት ስልት፡-




- ትኩረት ለሚጥል ህመም እንዲሰጥ እና ለህሙማኑ አስፈላጊው ድጋፍ እንዲደረግ ከህመሙ ተጠቂዎች እና ከህመምተኛዉ ቤተሰቦች ጋር በመተባበር፣
- የሚጥል ህመም ህክምና እንዲስፋፋ፣ በበቂ ባለሙያዎች እንዲሰጥና የመድሀኒት አቅርቦት ችግር እንዲቀረፍ ከፌዴራል ጤና ሚኒስቴር፣ ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ፣ ከክፍለ ከተማና ወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች፣ ከሆስፒታሎች፣ ከክልል ጤና ቢሮ፣ በዞን እና በወረዳ ደረጃ ከሚገኙ ጤና ተቋማት ጋር ሰፊ ግንኙነት በመፍጠር እና በጋራ በመስራት፣
- በሚጥል ህመም ላይ ያለዉ የተሳሳተ አመለካከት እንዲለወጥ የቅስቀሳ ስራዎች፣ ስልጠናና ትምህርት ለተለያዩ አጋር ድርጅቶች ለምሳሌ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የማህበረሰብ ሰብ ክበቦች ለምሳሌ እድሮች ላይ ፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የግል ድርጅቶች፣ የእምነት ተቋማት እና ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በመስጠት ነው።

# ለታማሚዎች መብት መሟገት እና ድርጅታዊ ግንኙነቶችን ማዳበር

### ድጋፍ ሰጭ ቡድን (የህሙማን ተወካዮች) መመስረት

የችግሩ ባለቤት የሆኑትን የሚጥል ህመም ህሙማንና ቤተሰቦቻቸውን ተሳትፎ ለማጎልበት፣ ታማሚዎች በአገልግሎት ሰጭ ተቋማት በመድሃኒት አቅርቦትና በጤና ባለሞያዎች የሚገጥሟቸዉን የአሰራር ችግሮች እንዲፈቱ ለመስራትና በሚጥል ህመም ላይ ያለውን ተፅዕኖ ለመቀየር እንዲሁም ቤት ለቤት በመንቀሳቀስ ምክክሮችንና ግንዛቤዎችን ለመስጠት ድርጅቱ ህሙማንና ቤተሰቦቻቸውን አሰባስቦ ትርጉም ያለው ተጨባጭ ለዉጥ ለማምጣት እንቅስቃሴ ማድረግ የሚችል፥ መርሃ ግብር የሚያሰናዳ ድጋፍ ሰጭ ቡድን (የህሙማን ተወካዮች ኮሚቴ) ጥቅምት 25/2010 እንዲቋቋም አድርጓል።

# የኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ በጎ ፈቃደኞች

ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ ለበጎ ፈቃደኛ ባለሙያዎች እና ለተማሪዎች ማህበረሰቦቻቸውን የሚረዱበትን እድሎችን እና የስራ ልምዶችን ይሰጣል።

ወጣት በጎ ፈቃደኞቻችን በትምህርት ቤቶች ፣ በጤና ማዕከሎች ፣ በሆስፒታሎች ፣ በጎዳናዎች የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን በመጻፍ እና በመበተን እንዲሁም ግንዛቤ ማስጨበጫ ሙዚቃና ትእይንት በመስራት ይሳተፋሉ።

በተጨማሪም በህክምናዉ ዘርፍ የተሰማሩትን ሃኪሞች እና የመንግስት ተቋማትን በማግባባት አቅም የሌላቸዉ ህሙማን የምርመራ አገልግሎትና በአስፈላጊ ሁኔታዎች የሚረዱበትን መንገድ ያመቻቻል።













# የድርጅቱ አደረጃጀት እና አስተዳደር

ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ከዲሬክተሮች ቦርድ እና ከአማካሪ ኮሚቴ ጋር ይሠራል። ቦርዱ ሁሉንም የድርጅቱን እስትራቴጂ በማቋቋም ረገድ ንቁ ሚና የተጫወተ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በመተግበር ላይ ያሉ የስራ ፕሮግራሞችን በማስፈጸም ረገድ እገዛ እያደረገ ይገኛል። የቦርዱ አባላት ግልጽነት ያለውና ህጉን የጠበቀ የገንዘብ አያያዝ ፖሊሲዎችን በመተግበር ድርጅቱ ቀጣይነት ያለው የወደፊት ሕይወት እንዲኖረው ለማድረግና ተልእኮውን ለማሳደግ በቂ አቅም እንዳለው በማረጋገጥ ይሰራሉ። የህመምተኛ አማካሪ ኮሚቴ የታማሚዎቻችንን ፍላጎት እና ተግዳሮቶች በተሻለ ለመረዳት ከህመምተኞች እና ከቤተሰብ በቀጥታ መረጃ እና አስተያየቶችን ለማግኘት ቁልፍ መንገድ ናቸው። ታማሚዎችን በተሻለ ለመረዳት እንድንችልና የሚያስፈልጋቸውን በማወቅ አስፈላጊውን የድጋፍ አገልግሎቶችን ለሟሟላት ያስችለናል ።

## የድርጅቱ የቦርድ አባላት



ሲ/ር ቀለሟ ተስፋዬ
ክሊኒካል ነርስ ስፔሻሊስት



ዶ/ር ክንዱ ወልደሚካኤል
የህፃናት የነርቭ ሀኪም



ዶ/ር እፀገነት ፈጠነ ትዛዙ
የነርቭ ሀኪም




ወ/ሮ ሰዓዳ አወል
ንግድ

## የታካሚ እና የቤተሰብ አማካሪ ኮሚቴ



አቶ ክብሮም ሳህሌ
የልዩ ፍላጎት ባለሙያ



ወ/ት ሩት ብሩክ









# የድርጅቱ የሰው ሀይል

የኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ ሰራተኞች የ2012 ብሔራዊ የሚጥል ህመም ሳምንት ዘመቻ በተሳካ ሁኔታ በማጠናቀቃቸው ድልአቸውን በማክበር ላይ።

ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ ለስኬት ቁልፉ የአገልግሎት ተጠቃሚዎቻችን ፍላጎት ላይ ብቻ ማተኮር ሳይሆን ሰራተኞቻችንን እና በጎ ፈቃደኞቻችንን በጥሩ ሁኔታ መንከባከብ መሆኑን ያምናል።

ድርጅቱ ቋሚ ሰራተኞች እና በጎ ፈቃደኞች ያሉት ሲሆን ያለው የሰው ሀይል በጤና አገልግሎት መስክ ለምሳሌ ነርሶች፣ ሀኪሞች፣ የስነ ልቦና አማካሪዎች፣ የማህበራዊ ስራ ባለሙያዎች እንዲሁም በልዩ ፍላጎት ባለሙያ (special needs) እና አስተዳደር ፋይናንስ መስክ የረጅም ጊዜና በሙያው የካበተ ልምድ ያላቸው በቅን ልቦናና ፍላጎት የሚሰሩ በመሆናቸው የተሻለ አፈጻጸም እንዲኖረው አስችሎታል። እንዲሁም ሰራተኛው በስራው ደስተኛና ውጤታማ ሆኖ እንዲሰራ የሚያስችል አሳታፊ፣ አቅም የሚገነባ፣ የስራ ዕድገት ዕድል የሚፈጥር እና የሰራተኞችን ምርጫ ከግንዛቤ ውስጥ የሚከት ስርአት የተዘረጋ ከመሆኑም በላይ በስራ አመራሩና በሰራተኛው መካከል ጤናማ የስራ ግንኙነት በመኖሩ ድርጅቱ የተጣለበትን ሃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ አድርጎታል።

# የኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ
# የወደፊት ዕቅድ

- ስለሚጥል ህመም በቂ ግንዛቤ ያለው ማህበረሰብ መፍጠር
- የሚጥል ህመም ህክምናን ማስፋፋት እንዲሁም ማከም የሚችል ብቁ የጤና ባለሙያን ማብዛት
- የሚጥል ህመም ያለባቸው ታማሚዎችን አምራች፣ ጤናማ ዜጋ እንዲሆኑ ማስቻል
- ለታማሚዎቹ የሙያ ስልጠና መስጠት እንዲሁም ወላጆቻቸው በገቢ ማስገኛ ስራ እንዲሰማሩ ማዕከላትን ማቋቋም
- ታማሚዎች የሚደርስባቸውን ማህበራዊ ተፅዕኖ (ችግሮች) መፍታት እንዲችሉ የሚያግዛቸው የስነ-ልቦና ድጋፍ መስጠት
- ብሄራዊ የሚጥል ህመም ማህበር መመስረት እና እውቅና እንዲኖረው ማድረግ
- የሚጥል ህመም ያለባቸዉ ህሙማንና ቤተሰቦቻቸው ሰለህመሙ በቂ ዕውቀት እንዲኖራቸው ማስተማርና የአቻ ላቻ ግንኙነትን በማጠናከር እንዲደጋገፉ ማሰቻል
- የሚጥል ህመም ህሙማን በአገልግሎት ሰጭ ተቋማት በመድሃኒት አቅርቦትና በጤና ባለሞያዎች የሚገጥሟቸዉን
- የአሰራር ችግሮች እንዲፈቱ አብሮ መስራት
- ከጤና ተቋማት፣ ከመገናኛ ብዙሀን፣ ትምህርት ቤቶች፣ ከቤተእምነትና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር
- ሰለህመሙና ለህሙማኑ ሊደረግ ሰለሚያስፈልገዉ ድጋፍ የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት ማሰፋፋት
- የማሰተማሪያ ቁሳቁሶች ማዘጋጀትና ማሰራጨት (በራሪ ወረቀቶች፣ፖስተሮች፣ አጫጭር ቪድዮዎች...)

# ድርጅቱ ከሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች
# በተለየ መልኩ ያሉበት ተግዳሮቶች

**1. ትኩረት እየተሰጠው ያለ ማንም አለመኖሩ**
በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚጥል ህመም በሚሰጡ ሕክምናዎች ውስጥ ክፍተቶች መኖራቸውን ያሳያል ። እነዚህም የግንዛቤ እጥረት እና የመድኃኒት እጥረት ፣ የእንክብካቤ አገልግሎቶች እና መገልገያዎች እጥረት ይገኙበታል። የጤና ሚኒስትር እና የክልል ጤና ቢሮ ይህን ችግር ለመቅረፍ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑ።

**2. ድርጅታችን ብቸኛ ድርጅት መሆኑ**
ኬርኤፕለፕሲ ኢትዮጵያ የሚጥል ህመምን ብቻ ትኩረት አድርጎ የሚሠራ ብቸኛ ድርጅት መሆኑ እና ሌሎች ተመሳሳይ ስራ ላይ ያሉ ድርጅቶች አለመኖራቸው የድርጅታችንን ዓላማዎች ይበልጥ ለማሳደግ፣ አዳዲስ ክህሎቶችን ለማግኘትና ልምድ ለመለዋወጥ፣ ወጪ ለማጋራት እንዲሁም ገቢ ለማመንጨት ተጽእኖ አሳድሮበታል።

**3. ህመሙ ከእምነት ጋር የተገናኘ እንደሆነ ስለሚታሰብ**
ህብረተሰቡ የሚጥል ህመምን ከእምነት እና ከክፉ መንፈስ ጋር የሚገናኝ አድርጎ ስለሚያስብ ብዙዎች በገንዘብና በቁሳቁስ ሊደግፉን የሚችሉ ድርጅቶች ከሚጥል ህመም ጋር ራሳቸውን ለማቆራኘት ፍላጎታቸው አናሳ በመሆኑ ሥራችንን ለመደገፍ ሲቸገሩ ይስተዋላል::

በሀገራችን ውስጥ በሚጥል ህመም ላይ ላሉት ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት፣ ታማሚዎቹንም አምራች ዜጋ ለማድረግና ከላይ የተገለጹትን ችግሮች ለመቅረፍ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላትና የሁሉንም ህብረተሰብ ድጋፍ ይጠይቃል።

# በወ/ት ተዘራወርቅ እስጢፋኖስ የተፃፈ ግጥም የሚጥል ህመም ታማሚ




ከሁሉ አስቀድሜ ሰላምታ በመስጠት
ለኬርኤፕለፕሲ መስራቾች በእውነት
ግጥሜን ጽፌአለሁኝ በደስተኝነት
ስላከበርኳችሁ ከአንጀቴ በእውነት

ይህ ትምህርታችሁ በስነስርአት
በደንብ ጠንክሮ ታማሚውንም ሰው ተረድቶት
ይህ መጥፎ በሽታ ሰይጣን ነው የሚለውን ትቶት
በልጄ ላይ መጣ እርግማን ልክፍት የሚለውን ትቶት
በእናንተ ድጋፍ ትምህርቱን አግኝቶት
የአንጎል በሽታ መሆኑን ተረድቶት
ትምህርቱ ቢቀጥል መልካም ነው በእውነት
ግንዛቤ ቢኖር የሰው ልጅ እውቀት
እና መስራቾቹ በርቱ በዚሁ ሂደት (2)

በተጨማሪም ደግሞ ብዬ የምላችሁ
ምክር ለተጎጂ ወገን መስጠታችሁ
በእውነት ደስ ይላል ጌታ ያክብራችሁ

ከዚህ በመቀጠል ለተጎጂ ወገን ብዬ የምላችሁ
እናንተም አይዟችሁ
ሁልጊዜም በስርአት ምክሩን ይዛችሁ
በህክምና አለም ከተጣጣራችሁ
መድሀኒታችሁን በስርአት ወስዳችሁ
ሳትሰለቹና ሰዓት ሳታዛቡ ከተጠቀማቹ
ጭንቀት ብስጭትን እያስወገዳችሁ
ታማሚ ይድናል ብላችሁ ካላችሁ
እድሜ ልክ ቢሆንም ቀን ቢረዝምባችሁ
አይዟችሁ ይድናል ብዬ የምላችሁ
በተረፈም ደግሞ እግዚአብሔር ይዳብሳችሁ
ብዩ ጨርሻለሁ ለማስታውሳችሁ

# በትዕግስት ገበያዉ የተፃፈ ግጥም
# የሚጥል ህመም ታማሚ




እንደምን ቆያችሁ
የኢፕለፕሲ ማህበር ዝግጅት ተካፋይ የሆናችሁ
ተመስገን ነው አሁን
መድሎና መገለል ስለቀረልን
ማህበረሰቡም ግንዛቤ አግኝቶልን
በየቦታው በየመንደሩ
እየሆነልን ነው ሰው እሩሩ

ነርቫችን ተዛብቶብን ድንገት ሲጥለን
ይጠየፉናል አሞን እያዩን
አንዳንዱ ያግዛል እውቀቱን ተጠቅሞ
በኔም ቢመጣብኝ ብሎና አስቦ
ግን ይበዛል የሚያገለን

የሚጥል በሽታ ህጉን ከጠበቁለት
ከምንም አይቆጠርም አጋናችሁ አትዩት
ጭንቀትን በመርሳት
መኖር እንችላለን በትጋት
ማንም እንደሚኖረው በህይወት




# እርስዎን በመርዳት ደስተኛ ነን!

አድራሻችን፡-
ከደንበርዋ ኤም ሲ ኤች ሆስፒታል ቀጥሎ ቶጎ ጎዳና በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 897 አዲስ አበባ

ተንቀሳቃሽ ስልክ: +2519 1163 3077/ 0975 26 41 21/ 0940 26 25 81
የመስመር ስልክ:  +2511 16 69 44 55  ወይም አጭር የስልክ መስመር 9610
ድህረገፅ: www.careepilepsyethiopia.org ፌስቡክ:  ኢሜይል: ceo@careepilepsyethiopia.org

# የሚጥል ህመምም ይመለከተኛል !



CAREEPILEPSY ETHIOPIA

SAVING LIVES | CHANGING PERCEPTIONS